# የ43ኛው ጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር

# ሕግና ደንብ

## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

ህዳር 7/2018 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# 43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር
## አጠቃላይ መረጃ

- የውድድሩ ቀን፡- ህዳር 7/2018 ዓ.ም.
- የውድድሩ ቦታ፡- አዲስ አበባ ጃንሜዳ
- የውድድሩ ተሳታፊዎች፡- ክልል፣ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች፣የግል፣ ማዕከላትና ተቋም
- አዘጋጅ፡- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን


## አድራሻ

- ፖ.ሣ.ቁ 13336
- ፋክስ 251-11-6450879
- ኢ-ሜል eth@mf.worldathletics.org
- Website www.eaf.org.et

- ☎ 251-11-6479579
251-11-6479676
251-11-6479596
251-11-6479131
*ጉርድ ሾላ*
*አዲስ አበባ*


## ጥቅል ኘሮግራም

- *ህዳር 6/2018 ዓ.ም. የቴክኒክ ስብሰባ ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ*
- *ህዳር 7/2018 ዓ.ም. ውድድሩ የሚካሄድበት ቀን፤*

# የ43ኛው ጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ውድድር ሕግና ደንብ

**ዓላማ፡-**

- ክልሎችን፣ ከተማ አስተዳድሮችን፣ ክለቦችን፣የግል፣ የአትሌቲክስ ማመሠልጠኛ ማዕከላት በጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር በማሳተፍ ለአትሌቶች ዉድድር እድል መፍጠር፤
- በዉድድሩ አሸናፊ ለሚሆኑ አትሌቶች ሽልማት በመስጠት ለማበረታታት፤
- እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 10/2026 በአሜሪካ ፍሎሪዳ (ታላሃስ) ለሚካሄደው 46ኛው የአለም አገር አቋራጭ ውድድር ሀገር ወክለው የሚሳተፉ አትሌቶችን ለመምረጥ ነው፡፡

## *አንቀጽ አንድ*

## *አጠቃላይ የውድድሩ ደንብ*

1. **የውድድሩ መጠሪያ፡-** ይህ ውድድር 43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ውድድር ተብሎ ይጠራል፡፡
2. **ውድድሩ የሚመራው፡-** በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በአለም አቀፉ አትሌቲክስ (WA) ህግና ደንብ ይመራል፡፡
3. **ውድድሩን በበላይነት የሚመራ አካል፡-** የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

## *አንቀጽ ሁለት*

## *የውድድሩ ቀን፣ ቦታና ሰዓት*

የ43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር *ጥር ህዳር 7/2018 ዓ.ም.* አዲስ አበባ ከተማ ጃን ሜዳ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡

## *አንቀጽ ሦስት*

## *የውድድሩ አይነትና ርቀት /ካታጐሪ/*

የውድድሩ ዓይነት ኢንተርናሽናል የጃንሜዳ ሀገር አቋራጭ ሲሆን ከዚህ በታች በተገለጸው ካታጐሪ መሠረት ይከናወናል

**<u>በሴቶች</u>**

- ◊ በ"6" ኪ.ሜ ከ20 ዓመት በታች ሴቶች
- ◊ በ"10" ኪ.ሜ አዋቂ ሴቶች

**<u>በወንዶች</u>**

- ◊ በ"8" ኪ.ሜ ከ20 ዓመት በታች ወንዶች
- ◊ በ"10" ኪ.ሜ አዋቂ ወንዶች

**<u>በድብልቅ ሪሌ (Mixed relay)</u>**

- ◊ በ"8" ኪ.ሜ ወንዶችና ሴቶች

## *አንቀጽ አራት*

## *ድብልቅ ሪሌ /Mixed relay/*

በ43ኛው ጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ውስጥ የድብልቅ ሪሌ ዱላ ቅብብል ውድድር እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሴት እና ሁለት ወንድ ያሳትፋል፡፡ እያንዳንዱ አትሌት የአገር አቋራጭ አንድ ዙር (Each Running One loop of the curse) ይሮጣል/ትሮጣለች/፡፡ የአትሌቶች የአሯሯጥ ቅደም ተከተል በእያንዳንዱ ቡድን ይወሰናል፡፡ የቡድን ውጤት ወይም ደረጃ የሚወሰነው በቡድኖቹ አገባብ ቅደም ተከተል ነው፡፡

## *አንቀጽ አምስት*

## *የአትሌቶች የዕድሜ ገደብ*

1. ማንኛውም ዕድሜው ከ18-19 ዓመት የሆነ ማለትም /ከ1999-2000 ዓ.ም./ (እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31, 2006-2007) የተወለደ/ች አትሌት በወጣት ወይም በአዋቂ የውድድር ካታጐሪ መወዳደር ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ዕድሜው ከ16-17 ዓመት የሆነ ማለትም /ከ2001-2002 ዓ.ም./ (እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 31, ከ2008-2009) የተወለደ አትሌት በወጣት የውድድር ካታጐሪ ብቻ መሳተፍ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ዕድሜው ከ20 ዓመት እና በላይ የሆነ አትሌት ማለትም /1998/ ወይም (እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 31, 2005) በፊት የተወለደ በአዋቂዎች የውድድር ካታጐሪ ብቻ መሳተፍ አለበት፡፡
4. ዕድሜው ከ16 ዓመት በታች የሆነ አትሌት ማለትም /ከ2002 ዓ.ም./ (እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 31, 2009) በኋላ የተወለደ በውድድሩ ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

## *አንቀጽ ስድስት*

## *ተሳታፊዎች*

በ43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር የሚሳተፉ የክልል፣ የከተማ አስተዳድር፣ የክለብ፣ የማሠልጠኛ ተቋማት የግልና የሌሎች አገሮች ተወዳዳሪ አትሌቶች ናቸው፡፡

## *አንቀጽ ሰባት*

## *ቡድኖች የሚያስመዘግቡት ተወዳዳሪዎች ብዛት*

1. ማንኛውም ክልል ከተማ አስተዳድርና ክለብ በ6 ኪ.ሜትር ወጣት ሴት፣ በ8 ኪ.ሜትር ወጣት ወንድ፣ በ10 ኪ.ሜትር አዋቂ ሴት እና በ10 ኪ.ሜትር አዋቂ ወንድ በእያንዳንዱ ካታጉሪ ከ4 - 12 አትሌቶች እንዲሁም በሪሌ ዱላ ቅብብል (Mixed relay) ከ4-6 አትሌቶች ማስመዝገብ ይችላል፡፡

## *አንቀጽ ስምንት*

## *የምዝገባ ጊዜ*

1. የ43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ውድድር የተወዳዳሪዎች ምዝገባ ከጥቅምት 10 እስከ ህዳር 1/2018 ዓ.ም. ድረስ ነው፡፡
2. በውድድሩ የምዝገባ ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመዘገበ ክልል፣ ከተማ አስተዳድርና ክለብ ብር 3000 (ሦስት ሺ ብር) በመክፈል ህዳር 2/2018 ዓ.ም. ብቻ መመዝገብ አለበት፡፡
3. የምዝገባ ቦታ ጉርድ ሾላ በሚገኘው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽ/ቤት በተሰጡት የምዝገባ ቀናት ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ብቻ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ ዘጠኝ*

## *ስም ጥሪና መታወቂያ*

1. ተወዳዳሪ አትሌቶች በስም ጥሪ ቦታ ማንነታቸውን እና የክልል/የከተማ አስተዳደር ነዋሪ መሆናቸውን የሚገልጽ በዘመኑ የታደሰ መታወቂያ እንዲሁም የክለብ አትሌቶች የክለባቸውን ቴሴራ ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡
2. የተወዳዳሪዎች ስም ጥሪ ውድድሩ ከመጀመሩ ከ45 ደቂቃ በፊት ይከናወናል፡፡ የተወዳዳሪዎች ስም ጥሪ ከተከናወነ በኋላ በውድድሩ ላይ መሳተፍ አይቻልም፤ ተወዳድሮ የተገኘ አትሌት ውጤቱ ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ አስር

## የአትሌቶች ጤንነት

በውድድሩ ተካፋይ የሚሆን አትሌት ጤናው የተሟላ መሆን አለበት፤ ጤናው ያልተሟላ አትሌት ተሰልፎ ቢገኝና ጉዳት ቢደርስበት ተጠያቂ የሚሆነው ክልሉ/ከተማ አስተዳድሩ፣ ክለቡ እና ተቋሙ አትሌቱ ይሆናል፡

## አንቀጽ አስራ አንድ

## የነጥብ አሰጣጥ

1. በሁሉም የውድድር ካታጐሪ ከተመዘገቡት አስራ ሁለት አትሌቶች ውስጥ ቀድመው ውድድሩን ሳጠናቀቁ አራት ተወዳዳሪዎች (Top 4) ነጥብ ይሰጣል። ከአራት አትሌቶች በታች ደረጃ ያስመዘገቡ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች የቡድን ደረጃ ነጥብ ባይመዘገብላቸውም ባላቸው ውጤት መሠረት አትሌቶቹ በግል ይሸለማሉ።
2. ለእያንዳንዱ አትሌት በገባበት በግል ደረጃ መሠረት ውጤት ይመዘገባል። በቡድን ውጤት አሰጣጥ ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ ቁጥር የገባበት ደረጃ ተደምሮ አነስተኛ ነጥብ ያስመዘገበ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

**ምሳሌ፡-**

**ቡድን ሀ = 1ኛ" 5ኛ" 8ኛና 13ኛ ቢወጡ - ድምር - 27 ይሆናል**

**ቡድን ለ = 2ኛ" 3ኛ" 6ኛና 11ኛ ቢወጡ - ድምር 22 ይሆናል**

በዚህ ድምር ውጤት መሰረት አሸናፊ ቡድን "ለ" ይሆናል ማለት ነው። የውጤት ድምራቸው እኩል ቢሆን መጨረሻ ነጥብ ያስመዘገበ /ዘጊው አትሌት/ ማለት ለአንደኛው የቀረበው አትሌት ቡድን አሸናፊ ይሆናል

**ምሳሌ፡-**

**ቡድን ሀ = 1ኛ" 5ኛ" 8ኛ፣ 10ኛ ቢወጡ - ድምራቸው - 24 ይሆናል**

**ቡድን ለ = 2ኛ" 3ኛ" 6ኛ፣ 13ኛ ቢወጡ - ድምራቸው 24 ይሆናል**

ከላይ የተጠቀሱት 2 ቡድኖች ነጥባቸው እኩል ቢሆኑም ለአንደኛ የቀረበው የመጨረሻው /ዘጊው አትሌት/ 10ኛ የወጣ የ"ሀ" ቡድን ስለሆነ የ"ሀ" ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

## አንቀጽ አስራ ሁለት

## ክስና ይግባኝ ስለማቅረብ

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ1 ሰዓት በፊት ነው።
2. የውድድር ውጤቶችን ወይም የውድድር ተግባር ሂደትን በተመለከተ የክስ ጥያቄ የሚቀርበው ውጤቱ ይፋ በሆነ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው።
3. ማንኛውም የክስ ጥያቄ መጀመሪያ የሚቀርበው በቃል በአትሌቱ፣ በአሠልጣኙ ወይም በቡድን መሪው አማካይነት ለውድድሩ ዋና ዳኛ (Cross Country referee) ይሆናል። የውድድሩ ዋና ዳኛ ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ለዉድድሩ ዳይይሬክተር በማሳወቅ ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል።
4. በዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ አካል በጽሑፍ ከብር 1000.00 (አንድ ሺ ብር) ጋር ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ክስ ማቅረብ ይችላል። ክሱም በ30 ደቂቃ ጊዜ ውሳኔ ያገኛል።
5. ክሱ በክስ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርቶ ተገቢ ክስ ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ሆኖ ክሱ ተቀባይነት ይኖረዋል። ነገር ግን ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ብር ለፌዴሬሽኑ ገቢ ሆኖ ውሳኔው የፀና ይሆናል።

## አንቀጽ አስራ ሦስት

## አለባበስ

ማንኛውም ተወዳዳሪ የክልሉን፣ የከተማ አስተዳደሩን፣ የክለቡን/የተቋሙን የስፖርት ትጥቅ መልበስ አለበት፤ መለያ ለብሶ ያልቀረበ ተወዳዳሪ መወዳደር አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል እንዲሁም የክልሉን/የክለቡን መለያ ሳይለብስ ለሽልማት መቅረብ የለበትም፤ ቢቀርብም ሽልማት አይሰጠውም።

## አንቀጽ አስራ አራት

## የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት የመወዳደሪያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፣ ቁጥሩ የሚለጠፈው ግልጽ ሆኖ በሚታይ ቦታ በደረትና በጀርባ ላይ ነው። የመወዳደሪያ ቁጥር የሌለው በውድድሩ መሳተፍ አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል።

## አንቀጽ አስራ አምስት
## በውድድሩ ስፍራ በሰዓት መገኘት

ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ ከ45 ደቂቃ በፊት በውድድሩ ቦታ በመገኘት ለውድድሩ ዝግጁ መሆኑን ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳወቅ ይኖርበታል፤ በስም ጥሪ ቦታ ተገኝቶ ስሙን ለስም ጠሪ ዳኞች ያላሳወቀ አትሌት በውድድሩ ላይ መካፈል አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## የተወዳዳሪ መታወቂያ

የክልል/ከተማ አስተዳደር ተወዳዳሪ አትሌቶች በዳኞች ስም ጥሪ ቦታ ማንነታቸውን የሚገልጽ በዘመኑ የታደሰ መታወቂያ እንዲሁም የክለብ ተወዳዳሪዎች የክለባቸውን ቴሴራ ወይም ፓስፖርት ይዘው መቅረብ አለባቸው፤ ስርዝ ድልዝ ያለው መታወቂያ ወይም ቴሰራ ተቀባይነት አይኖረውም የግል ተወዳዳሪዎች ማንነታቸውን እና እድሜያቸውን የሚገልጽ ስርዝ ድልዝ የሌለው መታወቂያ ወይም ፖስፖርት ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት
## ጸረ-ዶፒንግ ምርመራ

በ43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ውድድር የዓለም አቀፉ ፀረ ዶፒንግ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ፀረ ዶፒንግ ኦርጋናይዜሽን ሕግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ከውድድሩ በፊት እና ከውድድሩ በኋላ የዶፒንግ ምርመራ ይከናወናል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## ሽልማት

1. ከ1ኛ - 3ኛ ለሚወጡ አትሌቶች የወርቅ፣ የብር እና የነሐስ ሜዳልያ ሽልማት ይሰጣል፡፡
2. በውድድሩ ከ1ኛ - 6ኛ ለሚወጡ አትሌቶች በአራቱም የውድድር ካታጎሪዎች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
3. በአራቱም የውድድር ካታጐሪ በቡድን ከ1ኛ-3ኛ ለሚወጡ ቡድኖች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
4. በድብልቅ ሪሌ (Mixed Relay) ከ1ኛ - 3ኛ ደረጃ ያገኙ ቡድኖች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
5. የቡድን አሸናፊ ለሚሆኑ ለአምስቱም ካታጐሪ ቡድኖች ለእያንዳንዳቸው የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፡፡

6. የአንጋፋ አትሌቶች ሽልማት በሁለቱም ጾታ ከ1ኛ-3ኛ ለሚወጡ የወርቅ፣ የብር እና የነሐስ ሜዳልያ እንዲሁም ከ1ኛ-6ኛ ለሚወጡ አትሌቶች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
7. ከተፈቀደለት የእድሜ ክልል ውጪ የተወዳዳሪ አትሌት ውጤቱ ይሰረዛል ሽልማትም አይሰጠውም፡፡

## *አንቀጽ አስራ ዘጠኝ*
## *የሥነ-ሥርዓት ጉድለት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ አሰልጣኝ፣ የቡድን መሪ፣ ወጌሻ ወይም ሌሎች የቡድን አባላት ውድድሩ በሚከናወንበት ወቅት የሥነ-ሥርዓት ጉድለት ካሣየና ውድድሩን በሚመሩ ዳኞች ወይም የውድድር አዘጋጆች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተዘጋጀው የአሠልጣኞች፣ አትሌቶችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ ሃያ*
## *የቴክኒክ ስብሰባ*

የቴክኒክ ስብሰባ ህዳር 6/2018 ዓ.ም. ከቀኑ 4፡00 ጀምሮ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ይካሄዳል፡፡

## *አንቀጽ ሃያ አንድ*
## *የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ቡድን ኮታ*

1. የትግራይ ክልል 22 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
2. አማራ ክልል 22 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
3. ኦሮሚያ ክልል 22 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
4. አዲስ አበባ አስተዳደር 22 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
5. ደቡብ ኢትዮጵ ክልል 20 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
6. ሲዳማ ክልል 20 ሰው ቡድን መሪና አሠልጣኝን ጨምሮ፤
7. ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል 15 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
8. ሐረሪ ክልል 10 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
9. ድሬዳዋ አስተዳደር 10 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
10. ጋምቤላ ክልል 8 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
11. አፋር ክልል 8 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
12. ሱማሌ ክልል 8 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ፤
13. ደቡ/ምዕራብ ኢትዮጵያ 20 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ ይሆናል፡፡
14. ማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል 20 ሰው ቡድን መሪና አሰልጣኝን ጨምሮ

ነገር ግን ከተሰጠው ኮታ በላይ ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ በራሱ ወጪ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

# የ43ኛው ጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር
## የተወዳዳሪ አትሌቶች መመዝገቢያ ቅጽ

**ክልል/ከተማአስተዳደር/ክለብማሠልጠኛማዕከል** ____________________________

| ተ.ቁ. | 6 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ሴቶች | ተ.ቁ. | 10 ኪ.ሜ. አዋቂ ሴቶች |
|---|---|---|---|
| 1. | | 1. | |
| 2. | | 2. | |
| 3. | | 3. | |
| 4. | | 4. | |
| 5. | | 5. | |
| 6. | | 6. | |
| 7. | | 7. | |
| 8. | | 8. | |
| 9. | | 9. | |
| 10. | | 10. | |
| 11. | | 11. | |
| 12. | | 12. | |
| **ተ.ቁ.** | **8 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ወንዶች** | **ተ.ቁ.** | **10 ኪ.ሜ. አዋቂ ወንዶች** |
| 1. | | 1. | |
| 2. | | 2. | |
| 3. | | 3. | |
| 4. | | 4. | |
| 5. | | 5. | |
| 6. | | 6. | |
| 7. | | 7. | |
| 8. | | 8. | |
| 9. | | 9. | |
| 10. | | 10. | |
| 11. | | 11. | |
| 12. | | 12. | |

| ድብልቅ ሪሌ (Mixed Relay) | |
|---|---|
| 1. | |
| 2. | |
| 3. | |
| 4. | |
| 5. | |
| 6. | |

ቅጹን የሞላው ስም ____________________________________________

ፊርማ ______________________

ኃላፊነት___________________________

ቀን ________________________________

# የተሳታፊ ልዑካን ማጠቃለያ

ክልል /ከተማ አስተዳደር/ ክለብ፣ ማሠልጠኛ ማዕከልና ተቋም
________________

ስልክ ቁጥር ________________ ኢ-ሜል ______________ ፋክስ
______________

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ተወዳዳሪዎች | | | |
| የቡድን መሪዎች | | | |
| የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎች | | | |
| አሰልጣኞች | | | |
| ሐኪም | | | |
| ፊዚዮ ቴራፒስት (ወጌሻ) | | | |
| **ድምር** | | | |

**ቅጹን የሞላው**

- ስምና ፊርማ ____________________
- ኃላፊነት ___________________
- ቀን _____________________

**ማ ሳ ሰ ቢ ያ፡- በ43ኛው የጃንሜዳ ኢንተርናሽናል አገር አቋራጭ ውድድር ላይ የሚሳተፉ አትሌቶች የሚከተሉትን አሟልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡**

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት ከ1ኛ-10ኛ ደረጃ ያገኙት በወንድም በሴትም ህዳር 8/2018 ዓ.ም. ኦሪጅናል ፓስፖርት እና ሁለት ጉርድ ፎቶ ፓስፖርት ሳይዝ መደቡ ነጭ የሆነ ይዛችሁ ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በውድድርና ተሳትፎ ክፍል ሪፖርት እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡
2. ፓስፖርት የሌላቸው አትሌቶች የልደት ሰርተፍኬት እና ሁለት ጉርድ ፎቶ መደቡ ነጭ የሆነ እና ፓስፖርት ዛይዝ ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በውድድርና ተሳትፎ ክፍል ሪፖርት እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡
3. በ6 ኪ.ሜ ወጣት ሴት እና በ8ኪ.ሜ ወጣት ወንድ ተሳታፊ አትሌቶች የወላጅ (አሳዳጊ) መታወቂያ ኮፒ ማሟላት አስፈላጊ ነው፡፡
4. አሠልጣኞችና የቡድን መሪዎች አትሌቶቻቸው ማሳሰቢያውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የማስተባበር እና እርዳታ እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡

# 43ኛው ጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሀገር አቋራጭ ውድድር ኘሮግራም

**ቀን፡ - ህዳር 7/2018 ዓ.ም.      ቦታ፡ - አዲስ አበባ ጃንሜዳ**

| ተ.ቁ | ሰዓት | ክንውን | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|
| 1. | 12:15 | የውድድሩ ስፍራ ለተመልካቾች ክፍት ይሆናል | በኢት/አት/ፌዴሬሽን |
| 2. | 12:45 | የ8 ኪ.ሜ. አንጋፋ አትሌቶች ስም ጥሪ ይደረጋለ | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 3. | 1:00 | የ8 ኪ.ሜ. አንጋፋ አትሌቶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 4. | 1:30 | የድብልቅ ሪሌ ተወዳዳሪዎች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 5. | 1:45 | የ6 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ሴቶች የስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 6. | 2:00 | የድብልቅ ሪሌ ተወዳዳሪዎች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 7. | 2:30 | የ6 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ሴቶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 8. | 2:45 | የ8 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ወንዶች የስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 9. | 3:15 | የ8 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ወንዶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 10. | 5:25 | የ8 ኪ.ሜ አንጋፋ አትሌቶች ሽልማት ይሰጣል | *በሽልማት ኮሚቴ* |
| 11. | 3:30 | **የድብልቅ ሪሌ ተወዳዳሪዎች ሽልማት ይሰጣል** | **በሽልማት ኮሚቴ** |
| 12. | 3:45 | የ10 ኪ.ሜ. የአዋቂ ሴቶች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 13. | 4:00 | ***የ6 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ሴቶች ሽልማት ይሰጣል*** | ***በሽልማት ኮሚቴ*** |
| 14. | 4:20 | የ10 ኪ.ሜ. አዋቂ ሴቶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 15. | 4:40 | የ10 ኪ.ሜ. አዋቂ ወንዶች ስም ጥሪ ይጀመራል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 16. | 5:00 | ***የ8 ኪ.ሜ. ከ20 ዓመት በታች ወንዶች ሽልማት ይሰጣል*** | ***በሽልማት ኮሚቴ*** |
| 17. | 5:25 | የ10 ኪ.ሜ. አዋቂ ወንዶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 18. | 6:00 | ***የ10 ኪ.ሜ. አዋቂ ሴቶች ሽልማት ይሰጣል*** | ***በሽልማት ኮሚቴ*** |
| 19. | 6:20 | ***የ10 ኪ.ሜ. አዋቂ ወንዶች ሽልማት ይሰጣል*** | ***በሽልማት ኮሚቴ*** |
| 20. | 6:30 | ***የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል*** | ***በሽልማት ኮሚቴ*** |
| 21. | 6:35 | ***የውድድሩ ፍፃሜ ይሆናል*** | |

***የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን***